# ጊዜው አልቋል

ከኢህአዴግ ባለስልጣን

ይድረስ ለኢትዮጵያውያን፤

ስሜን ገልጬ ለመናገር ባልደፍርም አሁን ካሉት የኢህአዴግ ሹሞች አንዱ ነኝ ብል በቂ ነው።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ለዘመናት በራሷ መንግስታት በነፃነት የተዳደረች ሀገር ብትሆንም ዛሬም ህዝቧ የራሱን መንግስት በራሱ ፍላጎት እና ምርጫ የማቋቋም መብቱ ሌሎች በቅኝ ግዛት ሲገዙ ከነበሩት ሀገራት እንኳን በጣም ያነሰ ነው።

እኔና እኔን መሰሎች ኢህአዴግን ከመቀላቀላችን በፊት በህሌናችን ሲብላላ የነበረውን በደርግ መንግስት ወቅት የደርግን መንግስት አምባገነናዊነት እና አረመኔነት በመቃወም የተከፈለውን መስዋእትነት በማሰብ ሻዕቢያና ወያኔ ኢትዮጵያን ሲቆጣጠሩ ይዘውት የገቡት ፖሊሲም ሆነ የፖለቲካ ፕሮግራም የተከፋን ጫካ ውስጥ ለማነሳሳት እንጅ ሃገር ለመምራት የሚበቃ ፖሊሲም ሆነ የተማረ ሃይል እንዳልነበራቸው በመታዘብ ገና ከጅምሩ ሃገር ለመምራት ብቃቱ እንደሌላቸው ተገንዝበን ነበር።

ይህንንም እኛ ብቻ ሳንሆን አቶ መለስም ጠንቅቀው ሳላወቁ የመጀመርያ ስራቸው በወቅቱ ከህወሓት ከኦነግ እና ሻዕቢያ የድርጅት ብቃትም ሆነ የሰራዊት ጥንካሬ እንዲሁም የትግል ልምድ ሻዕቢያ በጣም የተደራጀ መሆኑና እነ አቶ ኢሳያስ በሻዕቢያ ውስጥ ሙሉ ስልጣን ያላቸው እና አጋሮቻቸው የሚያከብሯቸው ወይም የሚፈሯቸው ብቸኛ መሪ መሆናቸውን አቶ መለስ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ በአንፃሩም እራሳቸው አቶ መለስም ሆኑ የኦነጉ መሪ በየድርጅቶቻቸው ተቀናቃኝ እንዳለባቸው በመገንዘብ የአቶ መለስ የመጀመርያ ስራ ሻዕቢያ የሚፈልገውን በተሎ መስጠት እና ሻዕቢያን አቶ ኢሳያስን ማስደሰት እና የራሳቸው ደጋፊ ማድረግ ስለነበር ይህን በሚገባ ተወጥተው ሻዕቢያ ጀርባቸውን እየጠበቀላቸው ከፊት ለፊት የሚያደናቅፋቸውን እና ተቀናቃኝ ይሆናል የሚሉትን ሁሉ መምታት ጀመሩ። ስልጣናቸውንም አደላደሉ።

በዚህ ወቅት የወያኔ አካሄድ ያስደነገጠን ሁሉ ምርጫችን ሶስት ነበር፤

1. ወያኔን በትጥቅ ትግል ማስወገድ
2. በሰላማዊ መንገድ የፖለቲካ ፓርቲ አቋቁሞ ወያኔን መታገል
3. ወያኔን ተቀላቅሎ አባል ሆኖ መስራት ነበር የነበሩት ምርጫዎች።

እኔን መሰሎች በወቅቱ የትጥቅ ትግል የሚለውን አማራጭ ያልመረጥንበት ምክንያት ባጭሩ ወቅቱ አለም ባንድ ጎራ ብቻ ያለተቀናቃኝ የተያዘች በመሆኑ እና ይሄው ጎራም እነ አቶ መለስን የደገፈ በመሆኑ ትጥቃም ሆነ መጠጊያ ማግኘት የማይሞከር በመሆኑ ትጥቅ ትግል ብቁ አማራጭ አልነበረም።

ሁለተኛው አማራጭ ፓርቲ አቋቁሞ ከወያኔ ፈቃድ አውጥቶ በወያኔ ህግ የሚተዳደር ተቃዋሚ መሆኑ በደፈናው ወያኔን ለመርዳት ተቃዋሚ ፓርቲ አለ ለማስባል ካልሆነ በስተቀር የዲሞክራሲን ምንነት የማያውቀው እና የራሱን አባላት መብት የማያከብረው ወያኔ ለተቃዋሚው በህግ ይዳኛል ብሎ መገመት ብሎም በፖለቲካ ውድድር ባደባባይ እየተበለጠ ለተቀናቃኙ ፓርቲ አባላት መጠናከር ወያኔ

ዝም ብሎ ያያል ብሎ መገመትም በረሃ የነበረው ወያኔ ታሪክ እንደሚያሳየው ዝም ብሎ እራሱን አሳልፎ መስጠት ነው ብለን ነበር የደመደምነው። አስመሳይ ተቃዋሚም መሆን አልወደድንም።

ሶስተኛው አማራጭ የወያኔ አባል ሆኖ መታገል የሚለው ነበር። የኛ አማራጭ በደርግ መንግስት ስለአልተሞከረ በውቅቱ ደርግን ስልጣኑን ሳንቀናቀን በየሞያችን ብንሳተፍ የፓርቲውም አባል ሆነን ቀስበቀስ የአባላቱን የፖለቲካ እውቀት ብናዳብር እራሱን ኢሰፓን በተማሩ ኢትዮጵያውያን ብንገነባው ይህን ስናደርግ ለመሪዎች ስልጣናቸውን ሳናስፈራራ ህዝባችን ብናስተምረው ሌላው ቢቀር ሶቭየት ህብረት በወደቀችበት ወቅት ወያኔም ሆኑ ሻዕቢያ ብቸኛ አማራጭ ሆነው ባልቀረቡ ነበር። እራሱ ኢሰፓም ለአሜሪካ እንደ አማራጭ የመታየት እድል ነበረው። ምክንያቱም አሜሪካ በወቅቱ ኢሰፓን እንደ አማራጭ ያላየችበት ትልቁ ምክንያት በውጭም በውስጥም የነበሩ ምሁራን በሙሉ የኢሰፓ ተቃዋሚ በመሆናቸው እና ኢሰፓ ውስጥ ምሁራን ባለመኖራቸው መሆኑ የሚዘነጋ አልነበረም። ወያኔም በወቅቱ ማርክሲስት ስለነበር ለአሜሪካ የፖለቲካ አስተሳሰባቸው ያው ደርግ ማለት ነበር። ትልቁ የወያኔ አድቫንቴጅ ሙሁራን በሙሉ የደርግ ተቃዋሚ መሆናቸው ነበር። በወቅቱ ወያኔና ሻዕቢያ ያለ ጠንካራ የሙሁራን ተቃውሞ ካማራጭ ጦር ጋር በመቅረባቸው ነበር አሜሪካ የመረጠቻቸው። ይህ የእኔና እኔን መሰሎች እምነት ነው። ከዚህ እምነት በመነሳት የወያኔ አባል ሆኖ በደርግ ያላደረግነው መሞከር ነበር ምርጫችን። ለዚህ ምርጫም መንገዱ ቀላል ነበር። ምክንያቱም ወያኔ ታማኝ ሙሁራን ይፈልግ ስለነበር ወያኔ ውስጥ መግባት ብቻ ሳይሆን ስልጣን ማግኘትም ቀላል ነበር። የሚገርመው አቶ መለስም ከጫካ የመጡት ባልደረቦቻቸው ለስልጣናቸው ዋና ተቀናቃኞች ስለማያምኗቸው የታጩት ሙሁራን በቀጥታ ያቶ መለስ ወገን ተደርገው ስለሚታዩ ሙሁር ከሆንክ አቶ መለስን በመደገፍ ብቻ ስልጣን ማግኘት ቀላል ነበር።

ከዚህ በኋላ ነበር ህልማችንን እውን ለማድረግ ህወሓትን ማማከር እና በተለይ ለተቃዋሚዎች አስተማማኝ ነፃ የመደራጀት እና የመወዳደር እድል እንዲኖር የተሰጠንን ስልጣን መጠቀም የጀመርነው። ካደረግናቸውም ተግባሮች ጥቂቶቹን ብንመለከት አንደኛ ከተቃዋሚ መሪዎች ጋር ትህትና የተሞላበት ውይይት በየጊዜው ማድረግ፤ የተለያዩ ውይይቶችን በማንሳት ከተቃዋሚዎች የሚነሳውን ጥያቄ በመደገፍ በስራ ላይ እንዲውል ማድረግ። ተቃዋሚዎች ያሳሰቧቸውን ችግሮች በፍጥነት መፍትሄ መስጠት፣ ባጠቃላይ ተቃዋሚዎች ደፈር እንዲሉ ትህትና ማሳየት ትልቁ አስተዋጾአችን ነበር።

ሁለተኛው በተቃዋሚዎች ላይ አላስፈላጊ ወከባና አፈና የሚያደርጉ መለስተኛ የወያኔ ካድሬዎችን እና ከኛ አነስ ያሉ ባለስልጣናትን መገሰጥ እና ተቃዋሚዎችን በአክብሮት እንዲመለከትዋቸው ፈርጠም ያለ ድጋፍ ለተቃዋሚዎች ማሳየት ዋናዋናዎቹ ነበሩ። እነዚህም አስተዋጾዎች ቢያንስ ተቃዋሚው እራሱን እንዲደራጅ ደጋፊዎችን እንዲያስተምር እድል ሰጥተዋል። በርግጥ በእድሉ የተጠቀመ ብዙ ሙሁር ስለአልነበር ውጤት አላመጣንም። እንዲያውም ተቃዋሚ የተባሉት እውነተኛ ህዝብን አስተባብረው ስልጣን እስከመውሰድ ድረስ የሚታገሉ ሳይሆኑ ተቃውሞን እንደስራ በመያዝ ታማኝ ተቃዋሚ ሆነው ደሞዝ ማግኘት ብቻ ነው አላማቸው። ባጭሩ ተቀጣሪ ተቃዋሚ ናቸው ብል እውነት ነው። ለዚህም መረጃው ቅንጅት እና ህብረቱ (ህብረቱ ስል ያሁኑንን ፓርላማ ያለውን ሳይሆን ዋሽንግተን ተጠናክሮ የመጣውን ማለቴ ነው) ሁለቱ ድርጅቶች ባጭር ጊዜ ያሳዩትን የህዝብ ተሳትፎ ሌሎች በ14 አመት በጭራሽ ያልሞከሩት መሆኑን የተመለከትነው ጉዳይ ነው።

ዛሬ ይህንን እንድፅፍ ያነሳሳኝ ከላይ የዘረዘርኩላችሁ ሁሉ እንዳለ ሆኖ 1997 ምርጫ እውነተኛውን ወያኔ እንድናይ አድርጎናል። ዛሬ ወያኔ ማለት አቶ መለስ ብቻ ሆኗል። ዛሬ አቶ መለስ ማለት ኮለኔል መንግስቱ ማለት ሆነዋል። ዛሬ አቶ መለስ እኔ እንዴት በስልጣን ላይ ለዘላለም እንደምንኖር አውቃለሁ፤ እኔን ብቻ ተከተሉኝ። አለበለዚያ ሁልህም ዋጋህን ታገኛለህ ማለት ጀምረዋል። ለምሳሌ በቅርቡ በተደረገ አንድ የከፍተኛ ባለስልጣናት ስብሰባ ላይ አቶ መለስ እንዲህ ብለው ነበር፤

> እናንተ የአማራው፣ የኦሮሞው፣ የደቡብ ተወካዮች ሃላፊነታችሁን አልተወጣችሁም። የአማራው ተወካዮች የማራውን ህዝብ፣ የኦሮሞ ተወካዮች የኦሮሞን ህዝብ፣ የደቡብ ተወካዮች የደቡብን ህዝብ ከጎናችሁ ማሳለፍ አልቻላችሁም። ይህ ደግሞ እኛን የትግራይ ተወላጆችን ህዝባችንን በሚገባ ከጎናችን እንዲቆም ስላደረግነው እኛን በተለየ ዘረኞች እና የተጠላን እንድንሆን አስተዋፅኦ አድርጋችኋል። ሌላው ቀርቶ ልጆቻችሁን ወደውጭ ስትልኩ የህወሓት አባላት ልጆች በሄዱበት ሃገር ሁሉ ህወሓትን ፈልገው ይቀላቀላሉ። ከህወሓት ጋር አብረው ይሰራሉ። የእናንተ ልጆች ግን እንኳን ወደየድርጅቶቻችሁ ሊሄዱ ይቅርና መጀመርያውንም ድርጅቶቻችሁ በውጭ ሃገር ጭራሽ ነፍስ የላቸውም። አብረን የምንሰራ ከሆነ ለዚህ አስቸኳይ መፍትሄ ከናንተ እጠብቃለሁ።

ሲሉ በቁጣ ተናግረው ስብሰባውን ለቀው ወጡ። ይህ ቁጣ ያስደነገጣቸው የአማራው፣ የኦሮሞውና የደቡብ ተወካዮች ዛሬ እንደአዲስ እንደታዘዙት ህዝባቸውን ከጎናቸው ለማሰለፍ ከፍተኛ እቅድ አውጥተው እየተንቀሳቀሱ ነው።

ወገኖች! ዛሬ የእናንተ ትግል መጠናከር አለበት። ወደዳችሁም ጠላችሁም ዛሬ ከምንግዜውም በላይ መደማመጥ አለባችሁ። ወያኔ ጉዞውን ጨርሷል። ከአሁን በኋላ በወያኔ ውስጥ ያለው ጉዳይ ማን ቀድሞ ያመልጣል ብቻ ነው። ነገር ግን አገር እና ህዝብ አደጋ ላይ እንዳይወድቅ በተለይ በውጭ ያላችሁ ታጋዮች በሙሉ የመተባበሪያ ጊዜያችሁ አሁን ነው። ሰሞኑን ስምንት ጀኔራሎችን ባንድ ቀን ቢሮዎቻቸውን እና ጠባቂዎቻቸውን ቀይረውባቸው፣ እኛ እኛም በአይነ ቁራኛ ውስጥ ነን። ነገር ግን ወያኔ ስንቱን ያስራል? ስንቱንስ ይገድላል? ጎበዝ ጊዜው አልቋል። ቸር ይግጠመን።

<u>ከኢትዮሚድያ አዘጋጅ፡-</u> ይህ ከላይ የተነበበው የባለስልጣኑ መልእክት በኢትዮሚድያ ታትሞ በለውጥ ዋዜማ ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲደርሰው በማለት የላኩልንን በዋሽንግተን ዲሲ የአዲስ ድምፅ ሬድዮ ዋና አዘጋጅ አቶ አበበ በለውን ከልብ እናመሰግናለን።